# የመዳኛ መርከብ

ዝናብና ባህር በሌለበት ሥፍራ ኖኅ ለምን ግዙፍ መርከብ እንደሚሰራ ለማንም ግልጽ አልነበረም። እብድ ነው እንዳይባል በዘመኑ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር ርቆ በኃጢያቱ ተውጦ እንደልቡ ሲኖር እርሱ ግን እግዚአብሔርን በመፍራት ቅዱስ ኑሮ የሚኖር አስተዋይ ሰው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል።
ይሁንና ምክንያቱን ለሚጠይቁት ሳይታክት የሚነግራቸው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር በዘመኑ በነበሩት ሰዎች ክፉት ኃጢያትና የተበላሸ ኑሮ ከማዘኑ የተነሳ ሰውን በመፍጠሩ እንኳ መጸጸቱን እንደነገረው ነበር። ስለዚህም በምድር ላይ ሊፈርድ ከኃጢያታቸው ለሚመለሱ ደግሞ ከጥፋት የሚተርፉበት የመዳኛ መርከብ አዘጋጅ እንዳለው አበክሮ ይናገራል።
ሆኖም ፍርድ እንደሚመጣ የሚያሳይ በዘመኑ ላይ የተከሰተ ምንም ምልክት ባለመኖሩ ደግሞ፣ ሰው ሁሉ ኖኅን እንደሞኝ ቆጥሮት በጥፋት ጎዳና ላይ መጓዙን ቀጠለበት። ኖኅ ይህ ሊሆን ያለውን ፍርድ መረዳት አቅቶት ወደ ሞት እየተጓዘ ያለው ሕዝብ ያሳዝነውና፣ አንዳንዴ ሥራውን ቆም አድርጎ ድምጹን ከፍ በማድረግ፣ "እባካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ይህ መርከብ ከኃጢያት ለሚመለስ ሁሉ መዳኛ እንዲሆን እግዚአብሔር ያዘጋጀው ነው" እያለ ይናገራል፤ ነገር ግን ጀመረ! ያን የተለመደ ጩኸቱን በማለት ማንም ጥሪውን ከቁም ነገር ሳይቆጥርለት ዘመናት አለፉ።
አንድ ቀን እግዚአብሔር ኖኅን እንግዲህ ቤተሰብህንና ከእንስሳትም ዘር ደግሞ ሁለት ሁለት እያደረግክ ይዘህ ወደመርከብ ግባ እንዳለው ሲናገር አማቾቹ እንኳ የሚቀልድ ነው የመሰላቸው። ኖኅ ቤተሰቡን ይዞ ወደ መርከቡ ከገባ በኋላ እግዚአብሔር በሩን ዘጋው። ድንገት ያልተጠበቀ ዝናብና ዶፍ ይወርድ ጀመር። ያኔ ነበር ሕዝብ ሁሉ የተደናገጠው። ለካስ እንደ ዕብደት ቆጥረውት የነበረው የኖኅን ስብከት ዕውነት እንደነበር በመረዳት ወደ መርከቡ ትልቁም ትንሹም ተጋፍቶ ለመግባት ሞከረ። ኖኅ በሀዘኔታ እየተመለከታቸው ሊረዳቸው ግን አልቻለም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለብዙ ዘመናት ታግሶአቸው ኖኅና ቤተሰቡ ከገቡ በኋላ በሩን ዘግቶት ነበርና ነው። ውሐው እየጨመረ ሄደ በመርከብ ውስጥ ያሉት ብቻ ሲቀሩ ፍጥረት ሁሉ በጥፋት ውሐ ተደመሰሰ።
ይህ ነገር ከተፈፀመ ከብዙ ዓመታት በኋላ ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር ይህ የመጨረሻ ዘመን የኖኅን ዘመን ይመስላል ብሎ አስተማረ። በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ ፥ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ ይበሉ ይጠጡ፤ ያገቡና ይጋቡም ነበር፣ የጥፋት ውሐም መጣ ሁሉንም አጠፋ

ሉቃስ 17፡26




ዛሬም ቀኑ መምሸት መንጋቱ፣ ዓመታትም መምጣቸውና መሄዳቸው ከወትሮው ምን የተለየ ነገር አለ? ያሰኛል። ከዚህ የተነሳ ዛሬ የሚሰበከውን የደህንነት ወንጌል እንደሞኝነት ስብከት በመቁጠር ሰው ሁሉ በእልከኝነት ልብ እየሄደ ሳያውቀው ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ፈንታ ወደ ሞት እየተጓዘ ነው።
እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ላይ ሞቶ ኃጢያተኛውን ሰው እንዲያድን ከሰማይ ከላከው 2000 ዓመት አለፈ።
እግዚአብሔር ዛሬም የምህረት ደጁን ክፍት አድርጎ ሁሉንም ሰው ይጣራል። የክርስቶስ ወንጌል በየስፍራው መሰበኩ የሚያመለክተው ይህንኑ ጥሪ ነው ።
ነገር ግን ይህ ጥሪ ሁልጊዜ የሚቀጥል ዕድል አይደለም። አንድ ቀን ደግሞ በድንገት እግዚአብሔር ኖህንና ሰምተው የታዘዙትን ወደ መርከቡ እንደሰበሰባቸውና የመርከቡን በር እንደዘጋው፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የደኅንነት ወንጌሉን ሰምተው በርሱ ያመኑትን ለመሰብሰብ ይመለሳል።ያን ጊዜ ግን ክፍት የነበረው የምህረት ደጅ ይዘጋል።
መጽሐፍ ቅዱስ የመዳን ቀን ዛሬ ነው ይላል።
በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤ እነሆ ፥ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው።2 ቆሮ 6፡2

ወገኔ ዛሬ የመዳን መርከብ ተዘጋጅቶልሀል ያም ጌታ ኢየሱስ ነው።
መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።

ሐዋ 4፡12

ለምን ጌታን እንደግል አዳኝህ ተቀብለህ ሊመጣ ካለው ዘላለማዊ ፍርድ አትድንም?